

# ከቀየዬ ወጥቼ ከተማ ስገባ


Lesley Koyi, Ursula Nafula

Brian Wambi

Dawit Girma


Amharic

Level 3




በመንደራችን ያለው መናኻሪያ በሰዎች እና በታጨቁ አውቶብሶች ተጨናንቆ ነበር። መሬት ላይ ሊጫኑ የተዘጋጁ በርካታ ቁሳቁስ ነበሩ። ረዳቶች አውቶብቻው የሚሄድበትን ቦታ በጩኀት ይጣሩ ነበር።




‹‹ከተማ! ከተማ! ልንወጣ ነው፤ የሞላ!›› እያለ ወያላው ሲጮህ ሰማሁ። አዎ ልሳፈርበት የምፈልገው አውቶብስ ይሄ ነበር።




የከተማ አውቶብሱ እየሞላ ነው፤ ነገር ግን አሁንም ሌሎች ሰዎች ለመግባት ይጋፋሉ። የተወሰኑት እቃቸውን አውቶብሱ ኪስ ውስጥ ይጭናሉ። ሌሎቹ ደግሞ በአውቶብሱ ውስጥ።



አዲስ ገቢ መንገደኞች ትኬታቸውን ቶሎ ቶሎ አየት እያደረጉ አውቶብሱ ውስጥ መቀመጫ ቦታ መኖሩን ያያሉ። ህጻኖቻቸውን ያቀፉ ሴቶች ለረጅሙ መንገድ ተመቻችተው ተቀምጠዋል።



በመስኮቱ አጠገብ ጥብቆ ገብቼ ተቀመጥኩ። ከኔ አጠገብ የተቀመጠው ሰው አረንጓዴ የላስቲክ ሻንጣ ይዟል። አሮጌ ነጠላ ጫማ ተጫምቷል፤ ልባሽ ኮት ለብሷል፤ የተበሳጨም ይመስላል።



በመስኮቱ አሻግሬ እየተመለከትኩ ወዲያው ያደኩበትን መንደሬን እየለቀኩ መሆኑን አስተዋልኩ። ወደ ግዙፍ ከተማ እየተጓዝኩ ነበር።



መኪናው ሞልቷል፤ ሁሉም መንገደኞች ቦታ ቦታቸውን ይዘዋል። ሻጮች አሁንም እየተጋፉ ሸቀጦቻቸውን ለመንገደኞች ለመሸጥ ወደ አውቶብሱ ይገባሉ። ሁሉም ሰው የሚገዛው ነገር ፍለጋ ይሄን ስጠኝ ያን ስጠኝ እያለ ይጯጯህ ጀመር። የሚያደርጉት ነገር ሁሉ ግን እኔን ያዝናናኝ ይዟል።



ጥቂቶቹ ተጓዦች የሚጠጣ ነገር ገዙ፣ ሌሎቹ ደግሞ የሚበላ ነገር ገዝተው ይበሉ ጀመር። እንደኔ ምንም ገንዘብ የሌለን ደግሞ ዝም ብለን እንመለከታለን።



ይህ ሁሉ ድርጊት አውቶብሱ የመነሳት ጩኸት ሲያሰማ ረገብ ይላል፤ ሻጮችም ለመውጣት እየተጣደፉ እግረ መንገዳቸውን ፈጠን ፈጠን እያሉ እየተጯጯሁ ይሸጣሉ።



ሻጮቹ ለመውጣት እርስበራሳቸው ይጋፋሉ። አንዳንዶቹ መንገደኞቹን ‹‹አንዴ ልለፍ›› እያሉ ሲወጡ ሌሎቹ ደግሞ ለመሸጥ የመጨረሻ ሙከራ ያደርጋሉ።



አውቶብሱ ሲነሳ እኔ በመስኮት በኩል ወደ አፈጠጥኩ። እንደው ወደቀየዬ ዳግም እመለስ ይሆን እያልኩ ተደነቅሁ።



መንገድ ላይ እየተጓዝን የአውቶብሱ ውስጥ በጣም ይሞቃል። ለመተኛት አስቤ አይኔን ጨፈንኩ።



ሃሳቤ ሁሉ ግን ወደቤቴ ነበር። እንደው እናቴ ደህና ትሆን ይሆን? እንደው ጥንቸሎቼስ ገንዘብ ያወጡ ይሆን? ወንድሜስ አስታውሶ ችግኞቼን ውሃ ያጠጣ ይሆን?



በመንገዴም አጎቴ በዛ ትልቅ ከተማ የሚኖርበትን ቦታ ስም አስታወስኩ። ሳንቀላፋ ሁሉ ይሄን ስም አነበንባለሁ።



ከዘጠኝ ሰዓታት በኋላ ወያላ ወደመጣሁበት መንደር ተመላሽ የሚጓዝ ሰው እየጮኸ ሲጣራ ነቃሁ። ትንሽ ቦርሳዬን ይዤ ከአውቶብስ ወረድኩ።



ተመላሹ አውቶብስ በፍጥነት እየሞላ ነው። ወዲያው ፊቱን ወደምስራቅ አዞሮ መመለስ ጀመረ። አሁን ለኔ እጅግ አስፈላጊው ነገር አጎቴ የሚኖርበትን ሰፈር ማፈላለግ መጀመር ነው።

# Storybooks Canada

storybookscanada.ca

## ከቀየዬ ወጥቼ ከተማ ስገባ

Written by: Lesley Koyi, Ursula Nafula
Illustrated by: Brian Wambi
Translated by: Dawit Girma

This story originates from the African Storybook (africanstorybook.org) and is brought to you by Storybooks Canada in an effort to provide children's stories in Canada's many languages.

This work is licensed under a Creative Commons
Attribution 4.0 International License.